# ማጠቃለያ

እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ሕግጋተ እግዚአብሔርን ለመመርመር ስንነሣ የዚህን ያህል ጥልቅ ትርጉም ያላቸውና ሁለንተናዊ የክርስትና ሕይወታችንን የሚመለከቱ አልመሰለን ይሆናል:: ቀስ በቀስ ወደእያንዳንዱ ሕግ ይዘት ስንገባ ግን የሕግጋቱን ጥልቀት፣ ስፋትና ክብደት በሚገባ ተመልክተናል:: በእነዚህ ሕግጋት ትንተና ፍጻሜ ደግሞ የበለጠ ያስተዋልነው በአንድ ላይ ተደምረው ሕግጋቱ ሁሉ ቢጨመቁ የሚወጣቸው ፍቅር ሆኖ ነው የተገኘው:: የሁሉም ሕግጋት የመጨረሻ ግባቸው ፍቅር ነው:: ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ «የትእዛዛት ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው» ያለው:: 1ጢሞ.1÷5 ለሮሜ ሰዎች::በጻፈው መልእክቱ «ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው» ብሏል:: ሮሜ 13÷8–10::

ሕግጋት ሁሉ በፍቅር የሚፈጸሙ ከሆነ ስለፍቅር ጥቂት በመጻፍ ማጠቃለሉ የሚመረጥ ሆኖ ተገኝቷል::

## ፍቅር ምንድን ነው?

ፍቅር አንድ ሰው ከሌላው ጋር በየዕለቱ የሚያደርገው ግንኙነት የሚመራበት በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ልባዊ መዋደድና ጥልቅ መንፈሳዊ ጸጋ ነው:: በሰዎች መካከል በሚኖረው መልካም ግንኙነት የተነሣ አንዱ ለሌላው የሚያደርገው መልካም ነገር ሁሉ ፍቅር ነው:: አንዱም ለሌላው የሚያደርገው ይህ መልካም ነገር /ፍቅር/ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው:: በዚህ የዕለት ተዕለት ግንኙነት ለተራበ ማብላት፣ ለተጠማ ማጠጣት፣ የተቸገረን መርዳት፣ ያዘነን ማጽናናት ይህን የመሰለው መልካም ምግባር ሁሉ ሰው ለሰው ካለው ፍቅር የሚመነጭ ነው:: በዚህ መሰል ተግባር ለሌሎች መልካም ያደረጉትን ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመጣ ጊዜ «የአባቴ ቡሩካን÷ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ:: ...ከሁሉ የሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስለአደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት» በማለት የከበረ ዋጋ እንደሚሰጣቸው በወንጌል ተናግሯል:: ማቴ.25÷34–40:: ሰውን መውደድና ሰውን መርዳት ፍቅር ነውና ከፍቅር አምላክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ዋጋን ያስገኛል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ... መልካም እናድርግ» ያለው በፍቅር የሚደረግ መልካም ነገር የሚያስገኘውን መንፈሳዊ ዋጋ በሚገባ ስለተረዳ ነው:: ገላ.6÷10::

ይህ ፍቅር የተባለው ለሰው መልካም መሥራት የሰውን ድካሙን ሳይቀር በመሸፈን መገለጥ የሚገባው ተግባር

ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን በተመለከተም «ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲህም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ::» በማለት የክርስቶስ ሕግ የሆነው ፍቅር በተግባር እንዲገለጥ አስተምሯል:: ገላ.6÷2:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጽኑ ፍቅሩ የተነሣ የሰው ልጆችን ሸክም ተሸክሞ ሞት የማይስማማው ሲሆን መዋቲ ሥጋን ተዋሕዶ ሞትን ድል እንደአደረገልን ሁሉ፤ የወገኑን ጉድለት ሁሉ በመታገሥ ወደ ድኅነት እንዲደርስ ማድረግም ፍቅርን በተግባር መግለጥ ነው::

ፍቅር በመላእክት ልሳን ከመናገር በላይ የከበረ ነው:: እውነተኛ ፍቅር ከዕውቀትና ከልግሥና ሁሉ ይበልጣል:: ፍቅር የተባለው ሰውን መውደድ የክርስትና ሕይወት መሠረት ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፍቅር ያልተቀመመና ያልጣፈጠ ገድልና ትሩፋት ሁሉ የማይጠቅም መሆኑን ከገለጠ በኋላ «ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቀናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር አያስታብይም፤ ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል፤ እንጂ ስለ ዓመፅ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል÷ ሁሉን ያምናል÷ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል÷ በሁሉ ይጸናል:: ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም::» በማለት ስለፍቅር ጠባይዓት ዘርዝሯል:: 1ቆሮ.13÷1–10::

በዚህ መሠረት ሰው ለሚያፈቅረው ቸርነትን ያደርግለታል፣ የሚወደውን ይታገሠዋል፣ አይንቀውም፣ አይቀናበትም፣ አይመቀኘውም፣ ያምነዋል፤ ስለዚህ የራሱን ሳይቀር ይተውለታል /ይሰጠዋል/:: የሚወደውን ሰው እንዳያጣው በትሕትና፣ በየዋህነትና በትዕግሥት በጥንቃቄም ያፈቅረዋጠል:: ኤፌ.4÷2:: ሰው ሁሉ ለሚወደው ቸርና ርኅሩኅ ነው፤ ካለው ሁሉ በልግሥና ያካፍለዋል፤ በማንኛውም ነገር ቢሆን አይጨክንበትም:: ኤፌ.4÷32::

በእግዚአብሔር የሚታመን ክርስቲያን ሁሉ የፍቅር ሰው መሆን ይጠበቅበታል:: በመስቀል ላይ ለቤዛ ዓለም የተሰቀለው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሚገባ ነው:: አማናዊው የክርስትና መሠረት እምነትና ትምህርትም በዚህ ፍቅር መገለጥ ይኖርበታል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ «በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ÷ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና::» ሲል ያስተማረው ለዚህ ነው:: ገላ.5÷6:: ይህም እምነትን የሚያንቀሳቅሰውና በምግባር እንዲገለጥ ሥራም እንዲሠራ የሚያደርገው ሞተር ፍቅር መሆኑን ያስረዳል::

ከዚህም ሌላ ለመንፈሳዊ ነፃነት የተጠሩበት የክርስትና እምነታቸው በተለያዩ የሥጋ ፈቃዳትና ፈተናዎች እንዳይሰናከልና ፍሬ አልባ እንዳይሆን ሲያስጠነቅቅ «ወንድሞች ሆይ÷ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይስጥ÷ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ::» በማለት እምነታቸውን በመዋደድ

እንዲገልጡት መክሯቸዋል:: ገላ.5÷13:: ሃይማኖትን በም ግባር ለመግለጥ ፍቅር እጅግ አስፈላጊ መሣሪያ መሆኑን ሲያስገነዝብም «ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብት በላሉ እርስበርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::» ብሏል:: ገላ.5÷14:: ከዚህ ሁሉ በመነሣት ፍቅር የእምነት ተግባራዊ መግለጫ ነው ለማለት ይቻላል::

በሰዎች መካከል ፍቅር አለ ማለት በመካከላቸው ፍጹም የሆነ አንድነትና መናበብ አለ ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ ሰዎች በአንድ ፍቅር ይኖራሉ፣ አንድ ነገር ያስባሉ፣ በአንድ ዓላማ ይሠራሉ፣ በአንድ መንገድ ይጓዛሉ፣ በጠቅላላው አንድ ልብ ይሆናሉ:: በአንድ ወንጌል ለአንድ ሰማያዊ አገልግሎት የተጠሩት ሐዋርያት ሃሳባቸው፣ ዓላማቸውና ግባቸው አንድ ነበርና ተስፋቸውን ሲጠባበቁ «በአንድ ልብ ሆነው ይተጉ ነበር»:: የሐዋ.1÷14፤ 2÷42፤4÷32::

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በመጨረሻው ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ÷ የሌላው መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ÷ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ» በማለት ማስተማሩ በፍቅር መካከል መለያየትን የሚያመጣ አንዳች ነገር እን ዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: 1ጴጥ.3÷8:: ስለዚህ ፍቅር ስንል የሚዋደዱትን ሰዎች ልባዊ አንድነት የሚያመለክት መሆኑን እናስተጠውል:: የዚህ ዓይነቱ ፍጹም የልቡና አንድነት ወይም ከልብ መዋደድ በጽኑ እምነት ላይ ከተመሠረተ ፍቅር የሚገኝ መንፈሳዊ ፍሬ ነው:: የእግዚአ ብሔር ማደሪያ ካልሆነው ልብ ይህንን እውነተኛ ፍቅር ማግኘት አይቻልም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፍቅርን ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል የፈረጀው በዚሁ ምክንያት ነው:: ገላ.5÷22::

ፍቅር ከፍ ብሎ የተመለከትነውን ትርጉም ያዘለ ከሆነ የእግዚአብሔር ሰዎች በእምነት የሚኖሩትን ኑሮ በፍቅር መሠረትነት ላይ የተገነባ ሊያደርጉት ያስፈልጋል:: መምህረ አሕዛብ የተባለው ቅዱስ ጳውሎስ «በፍቅር ተመላለሱ» ካለ በኋላ «ፍቅርን ተከታተሉ» ማለቱ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: ኤፌ.5÷2:: 1ቆሮ.14÷1:: ሽንገላ የሌለበት ፍጹም ፍቅር የኃጢአት ጠላትና እንቅፋት ነው:: በሰዎች መካከል ፍቅር ካለ አንዱ በሌላው ኃጢአትን እንዳይሠራ የፍቅር ሕግ ያግደዋል:: ፍቅር በሰዎች መካከል ያለውን ክፋት የሚ ያስወግድ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ጥል ክርክርን ታስነሣለች፤ ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች::» በማለት የተናገረው ይህን የሚደግፍ ነው:: ምሳ. 10÷12:: ቅዱስ ጴጥሮስም «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ::» ማለቱ ፍቅር በኃጢአት ላይ ያለውን የበላይነት የሚያሳይ ነው:: 1ጴጥ.4÷8::

እንግዲህ የፍቅር መንፈሳዊ ጠቀሜታ ወሳኝ ከሆነ ሰሎሞን እንዳለው «የጎመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ

ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል።» ምሳ. 15÷17። በፍቅር ካልጣፈጠ ኑሮም ትርጉም አይኖረውም። ተድላንም፣ ደስታንም የሚያጣፍጣቸው፣ ችግርንም መከራንም የሚያቀልላቸው፣ ኑሮን ሁሉ ትርጉም የሚሰጠውና የሚያጣፍጠው የፍቅር ቅመምነት ነው። ስለሆነም የፍቅር ሰው መሆን በፍቅርም መኖር ተገቢ ነው። ሰው ሁሉ በፍቅር በመኖር የጠላት ዲያብሎስን ምሽግ ማፍረስና መሣሪያው ኃጢአትንም ኃይል አልባ ማድረግ ይችላል።

## ፍቅር በተግባር መተርጎም አለበት

ከዚህ በላይ ባሉት ክፍሎች የፍቅርን ጠቅላላ ፍችና ምንነት በዝርዝር ለማስረዳት ተሞክሯል። ከዚህ በኋላ በማንም አእምሮ ውስጥ ፍቅር ረቂቅ ከመሆኑ የተነሣ እንዴት በተግባር ይተረጐማል? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ስለሆነም በዚህ ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍት ፍቅርን በሥራ ላይ ስለማዋል የሚያስተምሩትን በመመርመር ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይሞከራል።

ነቢዩ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ÷ እነሆ÷መልካም ነው። እነሆም ያማረ ነው÷» በማለት ከተናገረው ቃል እንነሣለን። መዝ.132÷2። ነቢዩ በዚህ ቃል ከፍቅር የሚመነጭ መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ መተዛዘን፣ በጠቅላላው የልብ አንድነት ሊኖር እንደሚገባ አመልክቷል፤ የወንድሞች ኅብረትና አንድነት መልካም ያማረም ነውና። ይህ የሚገኘው ታዲያ ቀድሞ መዋደድ ያለ እንደሆነ ነው። ፍቅርም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ጸጋ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «ወዳጆች ሆይ ፍቅር÷ ከእግዚአብሔር ስለሆነ÷ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ÷ እርስ በርሳችን እነዋ ደድ።» በማለት በመካከላችን ሊኖር የሚገባው ምድራዊውና ኃላፊውን ጊዜያዊ ፍቅር ሳይሆን የማይጠፋ ዋጋ የሚገኝበት ሰማያዊው መንፈሳዊ ፍቅር መሆኑን አመልክቷል። 1ዮሐ.4÷7። በመቀጠልም ይህን ከእግዚአብሔር የሚገኝ /የሚሰጥ/ መንፈሳዊ «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።» ሲል መንፈሳዊው ፍቅር ፍጹም የሆነ የኅብረትና የአንድነት መሣሪያ መሆኑን አስረድቷል። 1ዮሐ.4÷8። ይኸው ሐዋርያ በሌላ ምንባብ ደግሞ እግዚአብሔርም በዚሁ ፍቅር እንደወደደንና አንድ ልጁን ለቤዛ ዓለም በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወት ይሆነን ዘንድ እንደሰጠን ከገለጠ በኋላ «ወዳጆች ሆይ÷ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።» በማለት በመፋቀር መኖር የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ግዴታቸው መሆኑን ገልጧል። 1ዮሐ.4÷11። ይህን ሃሳቡን የበለጠ ሊያጠናክረውና ስለ ፍቅር የሰዎችን ግዴታ አክብዶ ሲገልጽ «ማንም፡- እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወን

ድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።» ብሏል። 1ዮሐ.4÷20–21። በዚህ ትምህርቱም እርስ በርስ መዋደድ እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚገኝና ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን አስረድቷል።

በቅዱስ ወንጌልም «እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ...እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ።» በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው በሰዎች መካከል ያለው ፍቅር እርስ በርስ በመዋደዳቸው መገለጥ እንደሚኖርበት ለማስገንዘብ ነው። ዮሐ.15÷12–14። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ «የወንድማማች መዋደድ ይኑር።» ማለቱ የጌታችንን ትምህርት ተመርኩዞ ነው። ዕብ.13÷1። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ» በማለት በሰዎች ሁሉ መካከል ያሉ የወንድማማች መዋደድ በተግባር በሚታይ መንፈሳዊ ፍቅር መገለጥ የሚገባው መሆኑን አስተምሯል። 1ጴጥ.1÷22።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ሁሉ ሰማያዊ በሆነው መንፈሳዊ ፍቅር እርስ በርስ መዋደድ ከእግዚአብሔር የሚገኝ የተቀደሰ ስጦታ ነው። በጽኑ የክርስትና መሠረተ እምነት ላይ የታነፁ ሁሉ በዚህ ፍጹም ፍቅር ሊዋደዱ እንደሚገባቸው ያውቃሉ። መሠረታዊ የሆነ የክርስትና ትምህርትና ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ብስለት ከሌለ ስለዚህ ሰማያዊ ፍቅር ማወቅና መናገር አይቻልም፤ በዚህ ፍቅር መኖርም ከባድ ነው፤ የማያውቁትን በምግባር መግለጥ አይቻልምና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጽኑ ትምህርተ ሃይማኖት ላይ መመሥረታቸውን ለተሰሎንቄ ምእመናን ሲገልጽ «እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም» ብሏቸዋል። 1ተሰ.4÷9። ይህ የሚያመለክተውም ፍጹም መንፈሳዊ ፍቅር ከጽኑ የመንፈሳዊ ሕይወት አዝመራ የሚለቀም ጣፋጭ ፍሬ መሆኑን ነው።

ይኸው ሰማያዊ መንፈሳዊ ፍቅር የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመፈጸም የፈጣሪ ታማኝ አገልጋይና ወዳጅ የመሆን ማረጋገጫም ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ÷ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ ...እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ÷ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።» በማለት በወንጌል ያስተማረው ለዚህ ምስክር ነው። ዮሐ.13÷34–35። በዚህ ትምህርት መሠረት የእግዚአብሔር ወዳጅ ፍቅርና እርስ በርስ መዋደድ በተግባር መገለጥ አለበት። የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ማለት በአንደበት ብቻ ሳይሆን በሚታይ ፍቅር እርስ በርስ በመዋደድ በሥራ መተርጎም ይኖርበታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ ተዋደዱ።» በማለት ይህ ሰማያዊና መንፈሳዊ ፍቅር ፍጹምና ሸንገላ የሌለበት ሊሆን እንደሚገባ አስተምሯል። 1ጴጥ.1÷22–23። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለሮማውያን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ...በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» በማለት ስለ ፍቅር ተግባራዊ አፈጻጸም አስተምሯል። ሮሜ.12÷9–10። ለቆሮንቶስ ምእመናን ሲጽፍ ደግሞ «አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም። ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች /ግብዝነት በሌለው ፍቅር/ ራሳችንን እናማጥናለን» በማለት እውነተኛው ፍጹም ፍቅር ከግብዝነት የነጻ መሆኑን አስረድቷል። 2ቆሮ.3÷7።

ስለዚህ በወንድሞች መካከል የሚኖረው የእርስ በርስ ፍቅር በተወሰነ ጊዜ ታይቶ የሚጠፋ፣ በአንድ ወቅት ፈክቶ በሌላ ጊዜ የሚጠወልግ ወረት መሆን የለበትም። ከዚህ ይልቅ በጽኑ እምነት ላይ በቅሎ በጊዜው ሁሉ እያበበ መንፈሳዊ በረከትንና ረድኤተ እግዚአብሔርን እያፈራ የሚኖር ዘላቂ መሆን ይገባዋል። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ላሉ ክርስቲያኖች «እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።» በማለት የጸለየላቸው። 1ተሰ.3÷13።

ሐዋርያው እንዳደረገው ሁሉ ፍቅር እንዲጸና፣ እንዲያድግና ፍሬም እንዲያፈራ በጸሎት የታጠረና በጥንቃቄ የሚጠበቅ መሆን አለበት። ከዚህ በመነሣት ነው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ «ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ ...እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፤ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።» በማለት ፍጹም ሰማያዊ ፍቅር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሊጎዝ የሚገባው የክርስትና ሕይወት ማጣፈጫ እንጂ እንደገለባ እሳት ብልጭ ድርግም የሚል መሆን እንደሌለበት የሚመክረው። 2ጴጥ.1÷7። ስለሆነም ፍቅራችን ከግብዝነትና ከወረት ነፃ ሆኖ ሕግጋትን በመፈጸምና በማክበር በተግባር የሚገለጥ እንዲሆን መጸለይ ይገባናል። የሰሙትን የማይነሣ የነገሩትንም የማይረሳ ልዑል እግዚአብሔር ለቀደሙት አበው እንደተለመነ እንዲለመነን የፍቅር ሰዎችም እንዲያደርገን፣ በፍቅሩ በመጽናትም መንግሥቱን ለመውረስ እንዲያበቃን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

አነሣሥቶ ያስጀመረኝ፤ አስጀምሮም ያስፈጸመኝ ልዑል አምላካችን እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

ወይትባረክ እግዚአብሔር

ተፈጸመ